★ዴሞክራሲያ★

ዴሞ ቅፅ 34 ቁጥር 6 መጋቢት 2001 ዓ.ም

# የኅብረት ትግል ተመክሮና የኢሕአፓ አቋም

በዚህ ዓቢይ ርዕስ ላይ ኢሕአፓ በየጊዜው አቅዋሙንና እንቅስቃሴውንም ሲያቀርብ መቆየቱ የሚታወቅ ነው። በተለምዶ አነጋገር ድር ቢያብር አንበሳ ያስር ነውናም ታጋይ ኃይሎች መተባበራቸው ለድላቸው ወሳኝና ዋስትና ነው የሚለው ታምኖበት ኢሕአፓም ከተመሠረተ ከ1964 ዓ.ም. ጀምሮ በየጊዜው የኅብረት ጥረቶች አካል ሆኖ ተገኝቷል።

በአሁኑ ወቅት ይኸው የኅብረት ጥያቄ በአዲስ መልክ በፖለቲካው መድረክ ላይ ጎልቶ የመጣ በመሆኑም ካለፉት ተመክሮዎች በመነሳትና ደጉንም ስህተቱንም በመገምገም ኅብረት ስንል ምን ማለታችን ነው?' ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት እንሞክራለን። በቅድሚያ ግን ኢሕአፓ በየጊዜው የገባባቸው የኅብረት ጥረቶች በመሠረቱ በዋና ጠላት ላይ ያተኮሩና መለስተኛ የጋራ ስምምነትን መሠረት ያደረጉ እንደነበሩ መጠቀስ ያለበት ነው። በርዕዩተ ዓለም ደረጃ አንድ መሆንን ባለማስቀደምና ያለፈ ግጭትና ቁርሾንም በሁለተኛ ደረጃ በመያዝ ኢሕአፓ ከልዩ ልዩ ድርጅቶች ጋር በኅብረት ተያይዞ ለሕዝብ ትግል የተቻለውን አስተዋፅዖ አድርጓል። ነገር ግን ገና የደደቢቱ ጉድ ብቅ ካለ ጊዜ ጀምሮ ከዚህ ቡድን ጋር በኅብረት መተባበር ያልተቻለው ጠባቡ ወያኔ ኅብረ ብሔራዊ ድርጅቶችን በጠላትነት ፈርጆ ኅብረትን እንደ ታክቲክ/ዘዴ/ ክፍፍልን ግን እንደ ቋሚና ዘላቂ ዓላማው በመውሰዱ ነው። የኅብረት ግንባር ጠሪዎች ተንኮለኞች አማሮች ናቸው ባይ የነበረው ወያኔ ስለ ኅብረት መለፈፍ ሲጀምር ደግሞ በ1968 በእንግሊዝኛ ባወጣው ወይን በተባለው መፅሄት በብሔርና ኅብረ ብሔር ድርጅቶች መሀል ትብብር እንዲኖር ብሔር አቀፍ ድርጅቶች የብሔር ድርጅቶችን አብዮታዊነትና የሕዝባቸው ብቸኛ ወኪሎች መሆናቸውን አምነውና ተቀብለው በዚህ አካባቢ ማለትም የብሔር ድርጅቶች በሚንቀሳቀሱባቸው ወይም በጭቁን ብሔሮች ዘንድ ማንኛውንም ፖለቲካዊና ወታደራዊ እንቅስቃሴ ማድረግ የለባቸውም" ሲል ደምድሞ ነበር። ከትግራይ ውጡልኝ ጩኸቱን በጦርነት አጅቦ ወያኔ በኢሕአፓ ላይ መዝመቱንም

በኩራት ሲያቀርብ እንደነበር የሚታወስ ነው። "ህወሓት ኢሕአፓን በመውጋቱ በትግራይ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ትግል ላይ የተደቀነውን አንድ ከፍተኛ ጋሬጣ በመልቀሙ የትግራይን ሕዝብ ትግል ብሎም የኢትዮጵያን ሕዝብ ትግል አንድ እርምጃ ወደፊት እንዲራመድ አድርጎታል" ካለም በኋላ "ሕዝብ ጠላትና ወዳጅን አውቆ ትግሉን እንዲያፋፍም ማለትም ደርግ....የኢዲኅ ርዝራዦችና ኢሕአፓን ማጋለጥና ያለ ምህረት መደምሰስ ያስፈልጋል" ሲል ወያኔ "ኢሕአፓና የኢትዮጵያ አብዮት" በሚለው የ1976 "የማስተማሪያ ፅሁፍ" ባለው ውስጥ አስፍሯል። በመሆኑም እስከዛሬ የቀጠለው ይህ አለምህረት መደምሰስ አቅዋም የወያኔን ቀጣይ ፀረ ኢሕአፓነትን ይገልጣል።

ሕዝባችንና የኢሕአፓ አባላት የከፈሉትን የደም ግብር ከመጤፍ ሳይቆጥሩ ነጋ ጠባ ታሪክን ሊበርዙና በሀሰት ሊሸፋፍኑ የተነሱ ክፍሎች ኢሕአፓ ለኅብረት ጥሪ የራሱ ካልሆነ ጆሮ አይሰጥም የሚሉትን ተመክሮ ያስተባብላል። የምርጥ መኮንኖች መንግሥት በሚያዝያ 12 ቀን 1968 ዓ.ም. የአብዮታዊ ግንባር ይቋቋም ብሎ ላደረገው ጥሪ በወቅቱ በወጣው ዴሞክራሲያ ልዩ ዕትም ድርጅቱ የግንባር ጥሪውን በመሠረቱ መቀበሉን ካረጋገጠ በኋላ በዚሁ ግንባር መሳተፍ ያለባቸው ብሎ በወቅቱ የነበሩትን ድርጅቶችና ቡድኖች (ኦነግና ወያኔንም ጭምር) የሠራተኛውና የአስተማሪዎች፥ የገበሬውና የከተማ ቀበሌ ማኅበራት፥ በወቅቱ የነበረውን የሴቶች አስተባባሪ ኮሚቴ ወዘተ... በዝርዝር ከማቅረቡ ሌላ የግንባር ምሥረታው ውይይት ይጀምር ዘንድ ደርግ አፈናውንና ጦርነቱን ማቆም፤ የሕዝብን ዴሞክራሲያዊ መብት ማክበር፤ የታሰሩትን የፖለቲካ እስረኞች ሁሉ መፍታት አለበት ብሎ አቅዋሙን ገልፆ ነበር። ይህ ጥሪ ግን በደርግ ታምኖበት የተደረገ ባለመሆኑ ውጤት አልባ ሆኖ ወደ ተከሰተው አሰቃቂና የሽብር ሁኔታ መጓዛችን እውን ሆነ። ውይይቱም ከሕዝብ ጀርባ የሚካሄድ ሳይሆን ለሕዝብ ግልፅ ሆኖና ታውቆ መካሄድ እንዳለበትም ኢሕአፓ ገልፆ ነበር። ደርጉ ለውይይት ዝግጁ ካልሆነም ታጋይ ኃይሎችና ድርጅቶች በራሳቸው ግንባር ለመመስረት እንዲጥሩም ኢሕአፓም እንደጠራ ይታወሳል። " አብዮቱን ወደፊት ማራመድ የሚችል፤ ለአብዮቱ እድገት የጋት ታህል እንኳን መንገድ የሚከፍት ሁኔታ ከተፈጠረ ያንን ሁኔታ መርምረን መሠረታዊ እምነታችንን ሳንለቅ በዛ ሁኔታ ለመጠቀም መሞከር አብዮቱ ውስጥ የምንጫወተው ሚና የጣለብን ግዴታ ነው" በሚል የወቅቱ ዴሞክራሲያ ግልፅ አርጎ አስቀምጦታል። ድርጅቱ ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ይቋቋም፤ የመደራጀት መብት ላይ ገደብ አይደረግ ወዘተ... ብሎ ሲታገልም መሠረተ ሀሳቡ መተባበር የሚችሉ ሁሉ በጋራ የሀገርን ችግሮች ለመፍታት ይችሉ ዘንድ መብታቸው ይጠበቅ የሚል ነበር።

በየጊዜው የተሞከሩት የኅብረት ግንባሮች በደፈናው ፋይዳ ቢስ ናቸው ብሎ መደምደም ስህተት መሆኑ ግልፅ ነው። የመንግሥቱ ኃይለማርያም አገዛዝን ለመታገል ኢሕአፓ

ከኢዲኅ ጋር ኢዴአግ የተባለ ግንባርን መሥርቶ ታግሏል። አገዛዙ ሊወድቅ ሲቃረብም ከሎች ድርጅቶች ጋር (መኢሶንንም ጨምሮ) ኢዴኃቅን መሥርቶ በዚሁ ግንባርም አማካኝነት የሕዝብን ሥልጣን የነጠቀውን ወያኔንም ታግሏል። ይህ ሀገር አጥፊ ቡድን ሥልጣን ሲይዝ ኢሕአፓን አለምህረት መደምሰስ በሚለው አቅዋሙ መሠረት ኢሕአፓና ኢዴኃቅን አግልሎ የሽግግር መንግሥት ምሥረታውን ከማካሄዱ ሌላ በኢሕአፓ ላይ ያወጀውን የቆየ ጦርነት ገፍቶበት ለብዙ ህይወት መጥፋት ምክንያት ሆኗል። ሰላማዊ መፍትሄና ውይይትና ዕርቅን ፈልገው ለግዮኑ ጉባዔ የተጓዙትንም የኢዴኃቅ ወኪሎች አስሮ እስከዛሬም የልካኑን መሪ እንዳለቀቀ ሕዝብ የታዘበው ጉዳይ ነው። ኢዴኃቅ በኢዴኃኅ ወይም ኅብረት ተተክቶ ሕዝባችን ላደረገው ትግልና በተለይም ለ1997 ሉ ምርጫ ውጤት ያስገኘውንም ጥቅም መካድ የሚቻል አይደለም። በሌላ በኩል ግን ግንባሮቹ የተፈለገውን ድል ሳያስገኙ መፍረሳቸው ሐቅ ነው። ለምንና እንዴት? ምን ችግር እንቅፋት ሆነ? ምን ተመክሮስ ተገበየ ብለን መጠየቅ የግድ ይሆናል።

የለመደባቸው ከድርቅ እስከ ሰው ሰራሽ ችግር ሁሉንም በኢሕአፓ ላይ ማላከክ የሚቀናቸው ክፍሎች ግንባሮች የፈረሱት በኢሕአፓ ነው፤ ኢሕአፓ በፈለገውና በሚወስነው መንገድ የማይሄድ ግንባርን ያፈርሳል ወዘተ... እያሉ ሲከሱ ማድመጥ ተገደናል። የራስን ድክመት ለመመርምር ድፍረቱ ሲጠፋ ወይም በሌላ ማላከኩ የጮሌ ማምለጫ ሆኖ ሲገኝ ኢሕአፓን በሀሰት መወንጀሉ ልምድ መሆኑ አሳዛኝ ነው። ኢሕአፓ በገባባቸው ግንባሮችና ኅብረቶች ከሌሎች ድርጅቶች--ያውም ብዙ አባል ከሌላቸውም ጋር-- እኩል ድምፅ ማለትም አንድ ድምፅ ብቻ ይዞ የብዙሃኑን ውሳኔ እያከበረ የታገለ መሆኑ ይፋ ነው። ኢዴኃኅ/ ኅብረት / በሚመሠረትብት ጊዜ ዋናው አመራር በሀገራችን በሕጋዊነት በሚንቀሳቀሱት ድርጅቶች እንዲያዝ ሲደረግ ይህን ውሳኔ ኢሕአፓ ከመደገፉ ሌላ በ 1997 ሉ ምርጫ ኅብረቱ ሊሳተፍ ሲወስንም በምርጫው ሂደትና መጨረሻም ላይ ግልፅ ግንዛቤ የነበረው ኢሕአፓ ውሳኔውን ደገፈ እንጂ ተቃውሞ በራሱ አልሄደም። ይህ በእኩልነት የእኩል ድምፅ መያዝ የሚለው አቅዋምና አሠራር ምናልባትም አንዱ ችግር ፈጣሪ ጉዳይ መሆኑ መመርምር ያለበት ቢሆንም ኢሕአፓ ግን በኅብረት ከተያያዛቸው ድርጅቶች ጋር አብሮና ሰምሮ ለመሥራት ሙሉ ጥረት ማድረጉን ታሪክ የመዘገበው ነው። ከዚህ ሌላ ደግሞ ኢሕአፓ ያልገባባቸው ስብስቦች፤ ትብብሮችና ቅንጅቶች በራሳቸው ሲፈርሱ ለዚሁም ኢሕአፓን ለመውቀስ መነሳት ስህተት ከመሆኑ ሌላ ስንፍናና --ራስን ለመመርመር ድፍረትንም ማጣት--ነው።

መለስ ብለን የግንባር ወይም ኅብረት ተመክሮአችንን በምናይበት ጊዜ ሁሉም የተሞከሩት ከላይ መሆኑን እንገነዘባለን። ማለትም የድርጅት አመራሮች ተነጋግረውና ተስማምተው በድርጅቶች መሀል የሚፈጠሩ ግንባሮችና ቅንጅቶች ነበሩ። በመሆኑም ከላይ የተንጠለጠሉ

ተቋሞች ከመሆን ማምለጥ ካለመቻላቸው ሌላ የሚቀናጁት ድርጅቶች ደግሞ ሚዛናቸው ገለባ ከሆነ የኅብረቱ ሚዛን በአጠቃላይ ደግሞ የዶሮ ላባን ያህል መሆኑ አልቀረም። እኩል ድምፅ በሚለውም ፈሊጥ ትናንሽ ቡድኖች ሰብሰብ ብለው በትላልቆቹ ማለትም ብዙ አባላትና ተከታይ ባላቸው ላይ እየወሰኑ ይሄዱ ነበር ማለት ነው። ይህ የተዛባ ሂደትና እውነታ በኅብረት ውስጥ ኢሕአፓን በቅንጅት ውስጥ መኢአድን እየጎዳ መሄዱ ታይቷል። ይህ ከላይ ወደታች ሲቃኝ የቆየ የኅብረት ጥረት በመለስተኛ መርኅ ግብር መሠረት መሰባሰብ በሚል አቅዋማቸው መሠረታዊ ልዩነት ያለውን ሁሉ አግበስብሶ በማቀፉ ኅብረቱ በተባበረና በተቀናጀ መልክ ግልፅና የታመነበት የጋራ ዓላማ ይዞ ሊታገል እንዳይችል አግዶታል። ዘንግ ከተተከለ ልብ ከተከፈለ እንዲሉ አንዱ ካለው አገዛዝ ጋር ተቃቅፎና ተፈቃቅሮ ሊቀጥል እየዳከረ ሌላው ደግሞ ያለውን አገዛዝ ጠላት ብሎ ሊያወድቅ እየጣረ በአንድ ኅብረት መጠቃለሉ የባልቴት ወበራ ከመሆን አላለፈም። ባለፈው ምርጫ እንደታየው ሕዝብን ለመክዳት የወሰኑት የኅብረትም ሆነ የቅንጅት ክፍሎች ዶሮ ሳይጮህ ክህደታቸውን አቀላጥፈው ከወያኔ ፓርላማ ተብዬ በረት ገብተዋል። የነበሩባቸውን ስብስቦችንም ለማፍረስና ለመጉዳት ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል።

ኅብረት ስንል ብዙውን ጊዜ ክብደት ያልተሰጠው ሐቅ ግን የኅብረት ፖሊሲ፥ አቅዋምና ፖለቲካን በኅብረተ ሰቡ ዘንድ እውን ማድረግን ይመለከታል። ድር ቢያብር አንበሳ ያስር የተባለውን ስንቀበልም ድሩ ሕዝብ መሆኑን ማወቅና በገቢርም መቀበል አስፈላጊ ነው። የድርጅቶች መተበባር የሕዝብን በጋራ ዓላማና እንቅስቃሴ ዙሪያ መተሳሰርን ሊተካ አይችልም። የኅብረት ግንባር ፖለቲካን በመጀመሪያ ደረጃ በሕዝብ ዘንድ እውን ማድረግ የሚለው መርህ በዋናነት ደረጃ የሚጠቅሳቸው የሚከተሉትን ነው።

ሀ / ሰፊውን የሕዝብ ቁጥር ሊያሰባስብ የሚችል አቅዋምና መፈክሮችን ይዞ ሕዝብን ማደራጀትና ለትግል ማሰለፍ፤

ለ / ኅብረትን ከታች ወደ ላይ ማለትም ሕዝብን ያቀፈ ኅብረት ለማድረግ የሕዝብን የሲቪክና ሙያ ማኅበራት ሙሉ ተሳትፎ ማጠናከር አስፈላጊ ነው።

ማለትም ድርጅቶች ያውም ከማህተምና የተወሰኑ አመራር አባሎች ውጪ አባልም ሚዛንም የሌላቸውን ሰብስቦ ኅብረት ከማለት በቅድሚያ ሕዝብን ማሰባሰብና የሕዝብ ድርጅቶችን ማጠናከር ይገባል ማለት ነው። እያንዳንዱን የማኅበረሰባዊ ክፍል በነፃ እንዲደራጅ ሊቀሰቅሱትና የትግሉም እምብርት እንዲሆን ለማስቻል ድርጅቶች የሚያስፈልገውን ትብብር ሊለግሱት ይገባል። ሰፊውን ሕዝብ የሚያሰባስብ አቅዋምና መፈክሮች ማስፈለጋቸውን በተመለከተ በተጨባጩ የኢትዮጵያ ሁኔታ ቅድሚያ የሚሰጠው ሀገርን ከወያኔ የጥፋት ዘመቻ ማዳን የሚለው በመሆኑ ሰፊውን የሕዝብ ኃይል በዚህ ዙሪያ

ለማሰባሰብና ለማሰለፍ መጣር ማለት ነው። ሀገር ማዳን ማለትም ሕዝባችን ለረጅም ዓመታት ለመብቱና ለዴሞክራሲ ሲያደርግ የቆየውን ትግል ባቀፈ መልኩ እንጂ ዳግም ኢትዮጵያን ለጨቋኞች፣ ጠባቦችና ትምክህተኞች አሳልፎ ለመስጠት አይደለም። ኢትዮጵያን ማዳን ስንልም ኢትዮጵያ ላይ የመጣውን አደጋ በተመለከተ ግልፅ ግንዛቤ ያስፈልገናል። ለሰለባ የመጣ ልብስ ቢጥልሉት አይመለስ ነውና የመለስ ቡድን ሲመሠረት ጀምሮ ኢትዮጵያን ሰለባ ሊያደርግ ቆርጦ የተነሳ ነውና ምን ያህል ቢሰግዱለት ከዚህ ፀረ ኢትዮጵያ አቀዋም ከቶም ነቅነቅ የማይል መሆኑ መታወቅ አለበት ማለት ነው። በግንቦት 1997ሑ ምርጫና በተከተለው ቀውጢ ሁኔታ በዚህ መሠረታዊ ግንዛቤ ላይ ብዥታ በመስፈኑና የተቃዋሚ ድርጅቶች መሪዎች ነን ያሉ የተወሰኑት ከሕዝብ ሳይሆን ከወያኔ መሪዎች መመሳጠሩን በመምረጣቸውና ከእነ መለስ  ዜናዊ ባልተናነሰ የሕዝቡን ቁጣና መነሳሳት በመፍራታቸው ያ ትግል ሊደናቀፍ ቻለ ። የሙት ከተማው አድማ ተደርጎ በነበር የወያኔን አገዛዝ ደካማ ጎን ከማጋለጡ ባሻገር የሕዝብን ትግል ወደፊት ይገፋው እንደነበር አሌ ማለት አይቻልም። የግንባር ወይም የኅብረት ፖለቲካ ስንልም ብዙኃኑን በኅብረት የሚያሰልፍ ፖለቲካና መለስተኛ ልዩነቶችን በሚዛናቸው ይዞ ዋናውን ትግል እንዳያደናቅፉ የሚያደርግ ማለታችን ነው።

ከዚህ በተያያዘ ሕዝቡ በራሱ የሲቪክና ሙያ ድርጅቶች አማካይነት በፖለቲካው መድረክ ቦታውን ይዞ ግዳጁን ይወጣ ዘንድ ሙሉ ጥረት ማድረግ ተገቢ ይሆናል። በየካቲት አብዮት ወቅትና ደርግም ሥልጣን ከያዘ በኋላ የሠራተኛውና አስተማሪዎች ማኅበር፥ የቀበሌ ማኅበራት፥ የተማሪዎች ማኅበር፥ የአርሶ አደሮች ማኅበራት፥ የሴቶች ማኅበር፥ ዕቁቦችና ዕድሮች፥ የኡኡታ ኮሚቴዎች፥ የጭቁን ወታደሮች ማኅበር ወዘተ... ከፍተኛ ሚናን ተጫውተዋል። በፀረ ደርጉ ትግል ሰፊውሕዝብ ተሰባስቦ በኢሕአፓ ዙሪያ መታገሉ ዛሬ ሊካድ የሚችል ሐቅ አይደለም። "ጨቋኙ አገዛዝ ደካማ ነው ብለን አንዝናናም፣ ጠንካራ ነው ብለን አንሸማቀቅም፣ ሞኝ ነው ብለን አንቀልድም፣ ብልህ ነው ብለን አንሽቆጠቆጥም፣ ነገ ይውርዳል ብለን አናልምም፣ ይከርማልም ብለን አንባንንም፣ ተሸናፊ ነው ብለን አንቀናጣም፣ ነገር ግን አሸናፊ ነው ብለን ምንም ቢሆን ምንም አንቀበልም--ያለ ሰፊው ሕዝብ አሸናፊ የለምና ያለው ኢሕአፓ (ዴሞክራሲያ ታህሳስ 3/1968) ሕዝብን በሚያስተባብር መንገድ ቅስቀሳውን አካሂዶና ድርጅታዊ ሥራውንም አጠናክሮ የሕዝብን ትግል ሊያዳብር ችሏል። ከሕዝብ የተነጠሉና ከሕዝብ ማኅበራት፥ ተቋማትና ድርጅቶች የራቁ ወይም ያልተቀናጁ  ቡድኖች እርስ በርሳቸው የሚመሠርቱት ኅብረት ሆነ ትብብር ከመነሻው መጨረሻው አለማማሩ ግልፅ የሆነውም በዚህ የተነሳ ነው። ለዚህም ነው ከታች ወደላይ እንዲሉ ሕዝብን ያቀፈና ያሳተፈ የኅብረት ግንባር ፖለቲካን እውን ማድረጉ ላይ ድርጅቶች ማተኮር ያለባቸው። በሌሎች ሀገሮች ተመክሮዎች የታየው ሌላ ሐቅ ደግሞ

የአንድ ጠንካራ ድርጅት ማዕከልነት ለኅብረቱ መጠንከርና መቀጠል ትልቅ አስተዋፅዖ ሊኖረው እንደሚችል ነው። ሰፊ ግንባር
በሚል በአሁኑ ወቅት ሊተቃቀፉ የሚጥሩትን ቡድኖች እንደ ምሳሌ ብንወስድ ሁሉም ተደማምረው ሚዛን የማይደፉና በሀገራችን የነገ ዕጣ ላይ ምንም ጥላ ሊያጥሉ የሚችሉ አለመሆናቸውን እንገነዛባለን። ያለፉት የግንባር ጥረቶች የሚሰጡት ትምህርት አንድም ሚዛን ያላቸው ድርጅቶች በቅድሚያ የጥረቱ ማዕከል ወይም ምሰሶና ማገር መሆን እንዳለባቸው ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የሚተባበሩት በማን ላይ እንደሚተባበሩና ለምንስ መጨረሻ ወይም ግብ መሆኑን በሚገባ መረዳትና ማወቅ እንዳለባቸው ነው። ከጥቂት ዓመታት በፊት በመርህ ግብራቸው ጭራሽኑ ሊገጥሙ የማይችሉ መሆናቸው ብቻ ሳይሆን ተቃራኒ የሆኑ ድርጅቶች ትብብር ብለው የመሰረቱት ተቋም የጋራ ኢትዮጵያዊ ዓላማን ሳይሆን የአንዱን ድርጅት ብሔረተኛና የግንጠላ ዕቅድ ከግብ ሊያደርስ የተቃኘ ሆኖ በመገኘቱ እንኩቶ ሆኖ ቀርቷል። መድረክ በሚልም ደረጃ ብቅ ያለው የብሔረተኛ ስብስብ ዋና ዓላማ አፀያፊውን የወያኔ አገዛዝ በአዲስ መልክ ለማስቀጠል ከመሆኑ ባሻገር በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ እንደ መርገምትና የሰይጣን ቁራጭ የሚታየውን የብሔረሰብ ፌዴራሊዝምን ማለትም ሕዝብን በዘርና በቋንቋ የሚሸነሽነውንና የሚከፋፈለውን ፍልስፍና ሽንሽንና መርሆዬ ብሎ የተቀበለ ነው። የብሔረሰብ እኩልነት መብት በወያኔ የክልል ቀመር እንዳልተረጋጋጠ ደግሞ ምስክር ጥሩልኝ የሚል የሕዝብ ወገን የለም።

ኅብረት አስፈላጊ መሆኑ ክርክርን አይጋብዝም። ኅብረት ስንል ግን ድርጅቶች እርስ በርስ መጣመራቸውን ብቻ ወይም በዋና መልኩ የድርጅቶችን ማበር የሚመለከት አይደለም። ሀገር ወዳድ ድርጅቶች የኅብረት ፖለቲካ ማለትም ሰፊውን ሕዝብ ወደ ትግሉ የሚያሰባስብ አቅዋም ይዘው ሕዝብን ለማስተባበር ከተንቀሳቀሱ የኅብረት ፖለቲካ በሥራ የሚውል ይሆናል። ኅብረት ግንባር ከታች ወደላይም የሚለውን መሰረታዊና ትክክለኛ መርህ በሥራ ማዋል የሚቻልበትም ሁኔታ ይፈጠራል ማለት እንችላለን። የሕዝብ ድርጅቶችንና የሙያ ማኅበራትንም የትግሉና የትብብሩ አካል በማድረግ ከታች ወደ ላይ ሕዝብን ያቀፈ ኅብረትን መገንባት ይቻላል ማለት ነው። ኅብረት ስንል ኅብረት ሲሉ ልዩነቱ ከዚህ ባሻገር ደግሞ እነማን ለምን ዓላማ የሚለውንም መመልከቱ አይቀርም። በአሁኑ ጊዜ በሰፊ ኅብረት ሆነ በመድረክ ሽፋን ኅብረት ኅብረት የሚሉት ክፍሎች ከወያኔ አገዛዝ ጋር በምርጫ መሳተፍ በሚል ወይም በሰላማዊ ትግል ሽፋን ለመተቃቀፍ ወይም የወያኔን አገዛዝ ፖለቲካ አድሶ ለመቀጠል የተዘጋጁና የሚጥሩ ናቸው። በመሆናቸውም ከሕዝብና ከሀገር ጥቅም አንፃር ሁሉም አይውል ዋለብኝ በሚል ወግዱ የሚባሉ ናቸው። ድር ቢያብር የሚለውን ተግባራዊ ለማድረግ ከተፈለገ ሐቀኛ ሀገር ወዳድ ድርጅቶች ወያኔን ለማስወገድ በሚል ዓላማ ሕዝብን አስተባብረው ለማታገል መዋደቅ አለባቸው። ሰፊውን ሕዝብ የማስተባበሩ ጥረት

ሲያብብ ይህን መሠረት አድርጎ ድርጅቶቹም በተሻለ ትብብርና ህብረት ሊንቀሳቀሱ የሚችሉበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል። ኢሕአፓ በ1976 " ህወሓት- ኅብረት እንደ ታክቲክ፤ ክፍፍል እንደ ዓላማ/ስትራተጂ" ብሎ ባወጣው ፅሁፍ እንዳስፈረው "አንድነት የትግል ውጤት ነው። የሀገርንና የጭቁኑን ጥቅም ማስቀደምን የግድ ይላል። የፖለቲካ ብስለትን፤ ዴሞክራሲያዊነትን ለሕዝብ ፍላጎት ተገዢነትን ይጠይቃል። ትዕግስትና ውይይት፤ ለመግባባት መጣር፥ ኅብረትን ከልብ መሻት፥ በእኩልነት ማመን፥ የበላይነት መንፈስን ማስወገድ መኖር ያለባቸው ሁኔታዎችና እምነቶች ናቸው። ኢሕአፓ ኅብረት ሲል ኅብረት ለትግል፥ ኅብረት ለዴሞክራሲ በዴሞክራሲ፥ ኅብረት በእኩልነትና ለእኩልነት፥ ኅብረት ለሕዝብና ለሀገር ጥቅም ማለቱ ነው" ።

ለሕዝብና ለሀገር ጥቅም የማይበጅ ስብስብና ትብብር ወይም ኅብረት የማይፈለግ ጣጣ ፈንጣጣ መሆኑን ረጅሙ ትግላችን አሳይቶናልና ዛሬ ሀገር አድኑኝ ብላ በምትጮህበት ወቅት ልናስተናግደው የሚገባን ቧልት አይደለም። ኢሕአፓ ከላይ የተጠቀሱትን መርሆዎች አምኖባቸው ኅብረት ለመመረትና በኅብረትም ለመታገል ሀገርን አስቀድሞ ከፍተኛ ጥረትን አድርጓል፤ መስዋዕትነትንም ከፍሏል። ከድሉም ከውድቀቱም ትምህርትን ገብይቷል። ለዚህም ነው ሕዝብን አደናግረው፤ ብተናንና የበታኝ ሥራቸውን ቀና አስመስለው፥ ውሽልሽል ግባቸውን በሕዝባችን ላይ ሊጭኑ ቀና ቀና ያሉትን በጊዜ የምናጋልጣቸውና የምንቃወማቸው። ድር ሕዝብ ነው። ሕዝብ ካበረ የወያኔን አገዛዝ ያሸንፋልና የፀረ ወያኔ ድርጅቶች ዋና ግዳጅ ሕዝብን በወያኔ ላይ ማስተባበር ማደራጀት ነው።

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል!
እናቸንፋለን!!!